# ሙሽሪት ልመጂ

ተነግሯት ተነግሯት ፤ አልሰማ ስላለች
ከተቅበጠበጠች ፤ ያዋጣኛል ካለች
ላያዘልቅ ፍቅር ፤ ወዳ ከጀመረች
ዘመድ ሳታማክር ፤ እራሷን ከዳረች
ሁሉንም ፤ መቻል ነው ፤ ለምን ታለቅሳለች
ወዳ በገባችው ፤ ምን ታማርራለች ።

ላይፋቱ ማግባት ፤ አንዴ ካፈቀሩ
ንትርክ አያሻም ፤ በወግ ከተዳሩ
የምን ፤ ጭቅጭቅ ነው ፤ የምን እሹሩሩ
ወደድኩሽ ፤ ጠላሁሽ ፤ መቀበጣጠሩ
ማስተዋል ነበረ ፤ ቀለበት ሳታስሩ
ሽር ጉድ ፤ ሳይባል ፤ ጥንት ሳይሞሸሩ
ድንኳኑ ሳይጣል ፤ ድግሱን ሳትጠሩ ።

ተነግሮሽ ነበረ ፤ ቀድሞ ሳትሄጂ
ይሆነኛል ያልሽው ፤ አስቀያሚ ልጅ
እንኳን ፤ ላንቺ ቀርቶ ፤ ለናቱም አይበጅ
ቢለበልብሽም ፤ ቢያቃጥል ፤ ቢፋጅ
እንደ ፤ ማገዶ እንጨት ፤ እንደ ጧፍ ፤ ብትነጂ
እንግዲህ ፤ መቻል ነው ፤ ሙሽሪት ልመጂ
የሄድሽበት ቦታ ፤ የለም ያገር ልጅ
ቢጭኑሽ አህያ ፤ ቢፈጩበሽ መጅ
ጥሩ አገልጋይ ሆኖ ፤ መገዛት ነው እንጂ ።

ታዛቢው … March, 01, 2010